የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሀረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

## OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 18ኛ ዓመት ቁጥር 8<br>18th Year No. 8 | | ሀረር ጥር 23 ቀን 2005 ዓ/ም<br>HARAR, Jan,31/2013 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 1.00<br>Unit Price Birr 1.00 | በሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 952<br>P.O.Box 952 |


አዋጅ ቁጥር 116/2005 ዓ/ም

ማውጫ


የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርአት ቁጥር 6/1989 ለማሻሻል የወጣ አዋጅ........................................ገጽ 893


## አዋጅ ቁጥር 116/2005

## የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 6/1989 ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሀረሪ ሕዝብ ታሪክ ፣ ባህል የሀረሪን ማንነት የሚያንፀባርቁ ቅርሶችን እና የሀረሪ ቋንቋ በሚመለከት ፖሊሲዎችንና ህጎችን የማውጣት ስልጣን ያለው በመሆኑ፤

የጉባኤው ቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ስልጣን በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው አሁን ያለውን አደረጃጀት ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በተሻሻለው የሀረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 6/1989 ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 116/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

የሀረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 6/1989 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 (ሀ) (ለ) እና (ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው አንቀጽ 9(1) (ሀ)(ለ) ተተክቷል፡፡

"9(1)" ጉባኤው የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ. የባህል፣ የታሪክና ቅርስ ቋሚ ኮሚቴ እና

ለ. የቋንቋና ትምህርት ቋሚ ኮሚቴ፡፡

**3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሀረር ነጋሪ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሀረር ጥር 23 ቀን 2005 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዚዳንት